የኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን
ETHIOPIAN FOOD & DRUG AUTHORITY

ከኢትዮጵያ የምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

# የወባ መድኃኒት አግባባዊ አጠቃቀም

የወባ በሽታ በዓለም አቀፍ ደረጃ ዋና ከሚባሉት የሕዝብ ጤና ተግዳሮቶች አንዱ ነው።በተለይ ከሰሃራ በታች ባሉ የአፍሪካ ሀገራት ከባድ ጫና ፈጥሯል። በሽታው በኢትዮጵያም በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎችን ያጠቃ ሲሆን በተለይ በቆላማና በተፋሰስ አካባቢዎች ስርጭቱ ከፍተኛ ነው።

አገሪቱ ባለፉት ዓመታት የወባ በሽታን ለመከላከል ከፍተኛ ጥረት ስታደርግ ቆይታለች።የወባ በሽታን ለመቆጣጠርና ለማጥፋት ለአስርተ ዓመታት የተቀናጀ ጥረቶች ቢደረጉም የመድኃኒቶች ከበሽታ አምጪ ተሳክ ጋር መላመድ፣ ወጥነት የሌለው የጤና አጠባበቅ ተደራሽነትና መደበኛ ያልሆነ የመድኃኒት አጠቃቀም ያሉ ተግዳሮቶች ከፍተኛ ፈተና ሆነው መጥተዋል።

ውጤታማ ሕክምናን ለማረጋገጥና መድኃኒት የተላመደ የወባ በሽታ ስርጭትን ለመከላከልም የዓለም ጤና ድርጅትና የኢትዮጵያ ጤና ሚኒስቴር አግባባዊ የመድኃኒት አጠቃቀም ላይ በትኩረት በመስራት ላይ ናቸው፡፡

ወቅታዊና መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ ኢትዮጵያን ለወባ በሽታ ስርጭት ተጋላጭ የሚያደርጋት ሲሆን በዝናብ ወቅቶችም ሆነ በኋላ በተለይም በቆላማ፣ በወንዞችና በሐይቆች አቅራቢያ በሚገኙ አካባቢዎች ከፍተኛ የመተላለፊያ ፍጥነት አለ። የጤና ሚኒስቴር መረጃም፣ 60 በመቶ የሚጠጋው የአገሪቱ ሕዝብ ለወባ ተጋላጭ መሆኑንና በየዓመቱ ከ3 እስከ 5 ሚሊየን የሚገመቱ ሰዎች በሽታው እንደሚጠቁ ያመላክታል።

በኢትዮጵያ የወባ በሽታን የሚያስከትሉት ሁለቱ ዋነኛ የፕላዝሞዲየም ዝርያዎች ለአብዛኛዎቹ ሕመሞችና ሞት የሚዳርገው ፕላዝሞዲየም ፋልሲፓረምና በአንዳንድ ደጋማ አካባቢዎች በብዛት የሚገኘው ፕላዝሞዲየም ቪቫክስ ናቸው።

በኢትዮጵያ የወባ ስርጭት ወቅታዊ ሁኔታን የሚከተል ሲሆን ከፍተኛው የዝናብ ወቅቶች የወባ ትንኝ መራቢያ ቦታዎች ሲበዙ ነው። በአንፃሩ በቆላማ አካባቢዎች እንደ መስኖ ያሉ የግብርና ልማዶች በተወሰኑ ክልሎች ስርጭቱ እንዲጨምር አስተዋጽኦ አድርጓል።

የወባ በሽታ በኢትዮጵያ ነዋሪዎች ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ ከፍተኛ ሲሆን በጤና ላይ ብቻ ሳይሆን በኢኮኖሚው ምርታማነት ላይም ተጽዕኖ ያሳድራል።ምክንያቱም በሽታው በብዛት የሚከሰተው በእርሻና በአዝመራ ወቅት የግብርና ስራ በሚሰራበት ወቅት በመሆኑ ነው።

ኢትዮጵያ ውስጥ የወባ በሽታን ለመከላከል የሚደረገው ጥረት በአብዛኛው ትኩረት ያደረገው በሽታውን ለማከምና ለመከላከል ወሳኝ የሆኑ የፀረ ወባ መድኃኒቶችን በመጠቀም ነው። ጤና ሚኒስቴር የዓለም ጤና ድርጅት መመሪያን በመከተል የአርቴሜቴተር-ሉሜፋንትሪን (Artemether-lumefantrine) መድኃኒትን ያልተወሳሰበ የፕላዝሞዲየም ፋልሲፓረም የወባ በሽታን ለማከም የመጀመሪያ ደረጃ ምርጫ አድርጎ ጥቅም ላይ እየዋለ ይገኛል።

ከአርቴሜቴተር-ሉሜፋንትሪን በተጨማሪ ሌሎች በኢትዮጵያ ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉ የፀረ ወባ መድኃኒቶችን ስንመለከት ክሎሮኩዊን አሁንም በተወሰኑ ክልሎች ፕላዝሞዲየም ቫይቫክስ በተባለው ተውሳክ የሚመጠውን የወባ በሽታ ለማከም የመጀመሪያ ደረጃ ምርጫ ነው፡፡

ክሎሮኩዊን እና ፕሪማኩዊን የተባሉ መድኃኒቶች በጥምረት ሲወሰዱ የፕላዝሞዲየም ቫይቫክስ ኢንፌክሽኖች ላይ ዳግም መከሰትን ለመከላከልና ፈፅሞ ፈውስ ለማድረግ ይጠቅማሉ። የተሳካ የሕክምና ውጤቶችን ለማረጋገጥና መድኃኒት የተላመዱ ዝርያዎችን ስርጭት ለመከላከል እነዚህን መድኃኒቶች በትክክልና በአግባቡ ጥቅም ላይ ማዋል አስፈላጊ ነው።

ሆኖም ግን እንደ ሀሰተኛ መድኃኒቶች፣ ወጥነት የሌላቸው የአቅርቦት ሰንሰለቶችና የጤና አጠባበቅ ተቋማት ተደራሽነት ውስንነት ያሉ ተግዳሮቶች እነዚህን መድኃኒቶች በአግባቡ እንዳይጠቀሙ እንቅፋት ሆኗል።ስለሆነም የጤና አጠባበቅ ስርዓቱን ማጠናከር እና አግባባዊ የመድኃኒት አጠቃቀምን በሁሉም ደረጃዎች ማስፍን በጣም አስፈላጊ መሆኑን ያሳያል።

አግባባዊ የመድኃኒት አጠቃቀምን ማስፈን በኢትዮጵያ ውጤታማ የወባ ሕክምና የማዕዘን ድንጋይ ነው። ይህም ትክክለኛ የመድኃኒት አስተዛዝ፣ ትክክለኛ የመድኃኒት እደላና በአግባቡ የፀረ-ወባ መድኃኒቶችን መጠቀምን ያካትታል፣ በዚህም ትክክለኛው መድኃኒት በትክክለኛው መጠንና ጊዜ መሰጠቱን ያረጋግጣል።ይህ አካሄድ የሕክምናውን ውጤታማነት ከፍ ለማድረግ፣ የጎንዮሽ ጉዳቶችን ለመቀነስና መድኃኒትን የሚቋቋሙ የወባ ዝርያዎችን ለመከላከል አስፈላጊ ነው።

በምርመራ ሳይረጋገጥና ያለሐኪም ትዛዝ የፀረ ወባ መድኃኒቶችን መጠቀም በግለሰብም ሆነ በሕዝብ ጤና ላይ ከባድ መዘዝ ያስከትላል። የፀረ ወባ መድኃኒቶች አላግባብ ጥቅም ላይ ሲውሉ - ልክ ባልሆነ የመድኃኒት መጠን፣ ያልተሟሉ የሕክምና ሂደቶች፣ ወይም ያለ ትክክለኛ ምርመራ ጥቅም ላይ ሲውሉ ብዙ ችግሮች ያስከትላል፡፡

ከእነዚህ ችግሮች መካከል ከበሽታው በፍጥነት አለመዳን፣ የረዥም ጊዜ ሕመም መኖርና መድኃኒት የተለማዱ የወባ ዝርያዎችን መስፋፋት ዋና ዋናዎቹ ናቸው። በዚህ ዙሪያ በኢትዮጵያ አንዱና ዋነኛው ተግዳሮት ደረጃውን ያልጠበቀ ወይም ሀሰተኛ መድኃኒት መጠቀም ነው።ይሕም ብዙ ጊዜ መደበኛ ባልሆነ ገበያ የሚሸጡ መድኃኒቶችን መጠቀም የሚስተዋል ችግር ነው።

መድኃኒቶችን አላግባብ መጠቀም በሽተኛው በደም ውስጥ ያለው ጥገኛ ተውሳክ ረጂም ጊዜ እንዲቆይ፣ የመተላለፍ እድልና መድኃኒት የተላመዱ ዝርያዎች እንዲስፋፋ ያደርጋል።በተጨማሪም የጤና እንክብካቤ ተቋማት ተደራሽነት ውስንነትና ራስን የማከም ልምድ ከፍተኛ በመሆኑ ምክንያት የፀረ ወባ መድኃኒቶችን መደበኛ ባልሆነ መንገድ ለመጠቀም አስተዋጽኦ አድርጓል።

መሰል ተግዳሮቶች ለመፍታት የቁጥጥር ስርዓቱን ማጠናከር፣ የመድኃኒቶችን ጥራት በየጊዜው ማረጋገጥና የፀረ ወባ መድኃኒቶችን ትክክለኛ አጠቃቀም ለማሳወቅና ለማስገንዘብ ቀጣይነት ያለው የሕብረተሰብ ጤና ትምህርት ማከናወን ይጠይቃል።

በኢትዮጵያ በተለይም ከፍተኛ የወባ ስርጭት ባለባቸውና የፀረ ወባ መድኃኒቶች በብዛት በሚጠቀሙባቸው አካባቢዎች የመድኃኒት መላመድ አሳሳቢ ጉዳይ ነው። በተለይ መደበኛ ያልሆነ የመድኃኒት አጠቃቀም ባለባቸው ክልሎችና ሀሰተኛ ወይም ደረጃቸውን ያልጠበቁ መድኃኒቶች ስርጭት በሚታዩባቸው አካባቢዎች የወባ መድኃኒቶች ከበሽታ አምጪ ተውሳኮች ጋር የመላመድ ስጋት በከፍተኛ ሁኔታ እያደገ ነው።

ስለሆነም በኢትዮጵያ የወባ በሽታን ለመከላከልና ለመቆጣጠር አግባባዊ የመድኃኒት አጠቃቀምን ለማስፈንና ከመደበኛ የመድኃኒት አጠቃቀም ጋር ተያይዘው የሚመጡ ችግሮችን ለመፍታት ዘላቂ ስትራቴጂ ማዘጋጀትና በቁርጠኝነት መስራት የግድ ይላል፡፡

የወባ በሽታ ከፍተኛ የኅብረተሰብ ጤና ችግር ሆኖ ባለበት ኢትዮጵያ የወባ መድኃኒቶችን በትክክል ጥቅም ላይ መዋሉን ማረጋገጥ የሀገሪቱን የወባ በሽታ መከላከልና ማጥፋት ግቦችን ለማሳካት ከፍተኛ እገዛ ይደርጋል።

የጤና አጠባበቅ ሥርዓቱን ማጠናከር፣ ጥራት ያለው የመድኃኒት አቅርቦትን ማሻሻልና ኅብረተሰቡን በመድኃኒት አጠቃቀም ዙሪያ ማስተማር መድኃኒትን የተላመደ የወባ በሽታ ስርጭትን ለመከላከልና በሽታው የሚያደርሰውን ጫና ለመቀነስ ወሳኝ ነው።

Tel : +251-11-552-41-22
+251-11-552-41-22
P.o.box. 5681
Free call. 8482

http://www.fmhaca.gov.et/contact/
E-mail contactefda@efda.gov.et
Telegram channel link
https://t.me/ethiopianfoodanddrugauthority/

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ